# <u>የሰላማዊ ትግል በብዙሃን መጋናኛ ጭምር ታግዞ</u>
# <u>በወያኔ መቀልበሱ እና መዘዙ</u>

*"ለዘመናት የህዝባችን ብሶት የወለደው ጀግናው ኢሕኣዲግ ሰራዊት ደርግ  ሲጠቀምበት የነበረውን የኣዲስ ኣበባ ራዲዮ ጣቢያን ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል። ጉንቦት ሃያ ሽህ  ዘጠኝ ሞቶ ሰማኒያ ሶስት ኣመተ ምህረት"።*

እረወድያ "ፅድቁ ቀርቶብኝ በውጉ በኮነነኝ" ኣለ ያገሬ ሰው ያንዳንዱ ሽንገላ አልዋጥለት ሲል! እንዲህም አድርጎ የለ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ኢሕኣዴግ የኢትዮጲያን ብሄራዊ መገናኛ ኣገልግሎት ተቆጣጣረ። ይልቅ የኢትዮጲያን ቴላቪዝዮን እና ሬድዮን ወያኔ/ኢሕአዴግ ከሰው በላው ደርግ ነጠቀ ከዚያም የውሸት ውሽንፍር እና የሽብር ማዓት ሲረጭበት፣ ብሎም የኢትዮጲያን ህዝብ ሲያደናግርበት፣ የሰፊውን ህዝብ ልቦና ሲሰልብብበት ተስተውሉዋል በማለት ዛሬ ላይ ቆመን አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ይህም ወያኔ/ኢሕአዴግ እንደገቡልን ቃል ኪዳን ሳይሆን የኣብዮታዊ ደሞክራሲ ተልካሻ የፖለቲካ ትርፍ ለማገኘት የመገናኛ ብዙሃን እንደ ጠበል መርጫ እንዲሁም አልፎ ተርፎ ሲኖደሱን እና መጅሉስን እንደ ፖለቲካቸው ማጥመቂያ በማዋል ላይ ይገኛሉ። ይኽም ድርጊት የውያኔ/ኢሕአዴግ መሰሪ እና እኩይ ተግባር ኣንዱ መሆኑን የሚያጋልጥ ነው።

በ <u>ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ ም</u>  ኣሳይቶ ከነሳን ጊዜ ጀምሮ  ለሆዳቸው ያደሩ ጋዜጠኞችን ቀርቶ በኢትዮጲያ የህዝብ የመገናኛ ኣገልግሎት በሃገር መሪ ነኝ ባዮቹ በነመለስ ዜናዊ ጭምር የወያኔን ፖለቲካ የተቹ የተቀውሚ ድርጅት ኣባሎችን "መንገዳችሁን ጨርቅ ያድርግላቸሁ"፣ ለዘመናት ተከብሮ ለኣፍሪካ ጭምር የነጻነት መለያ  የሆነ ባንድራችንን "ጨርቅ እኮ ነው"፣ በመደጋገፍ አብረው የኖሩ ማህበረሰቦችን "ያይናችሁ ቀለም ኣላማረንም እና ከኢትዮጲያ ባስቸክዋይ ውጡ"፣ የሰለም እና እርቅ ጉባኤ በኢትዮጲያ ይጠራ ሲባሉ "ማን ተጣላ እና ነው" በማለት በሰላም ላይ ሲቀልዱ፣ የፖለቲካ ወይም የሃሳብ ተቃዋሚን በአሽሙር እስከ "ወራዳ" እያሉ በፓርላማ ውስጥ የተሰደቡበት፡ ታሪኩን እና ባህሉን የተወራረሰውን ኣንድ ህዝብ "ኣክሱም ለወላይታው ምኑ ነው"? መብቱን የጠየቀን ሁሉ "ሽብርተኛ እና ፀረ ሰላም" የመሳሰሉትን ጸያፍ ንግግሮች በመጠቀም እና ህዝብን በማሸማቀቅ ከመሪ የማይጠበቅ በዛኛው ዓለም ካሉት ፈልጭ ቆርጭ እንደ ጥሩ መልእክት በብቸንነት ወያኔ/ኢሕኣዴግ በሚጠቀምበት ሬድዮ እና ቴሌቪዝን ሰማንበት።

ሃገርን ያለማንገራገር ያስገነጠለ እና በርካሽ የሸጠ ብሎም ህዝቦቹዋን በማዋረድ ገዳምን እና መስጊድን የደፈረ ከአማላክ ጋር በማወዳደር ሃይማኖተኛ ነኝ ባዩ ኣዲስ የተሾሙት ጠቅላይ ሚንስቴር ደግሞ ጉድ ሳይሰማ መስከርም አይጠባም እንደተባለው" ዘላለማዊ ክብር ለመለስ ዜናዊ" በማለት በዚህኛው ዓለም በህይወት ካሉት ተከታይ የሙት ራእይ አስፈጻሚ በብሄራዊ መግናኛ ኣገልግሎት ሲነገርበት ኣይተናልም ሰምታናልም። መለስ ዜናዊ ስኳር የተወደደው "ገበሬው ሻይ መጠጣት ስለጀመረ ነው" እንዳላሉን ሁሉ ተተኪው የህሌና ታሳሪም "ጤፍ የተወደደው የኢትዮጲያ ሃዝብ የኑሮ ሁኔታ ስለተተሻሻለ እና የጤፍ ተጠቃሚ በመጨምሩ ነው" ብለውናል። ይህ ነው እንግዲህ ዶሮን ሲጃጅሉዋት በመጫኛ ጣሉዋት ማለት ሰፊውን ህዝብ ያደኸየ ግን የኣንድ የፖልቲካ ፓርቲን ያገዘፈ እና ዓይን ያውጣ ውሸት ያውም በመግናኛ ኣገልግሎት በኩል እንደገና መደገም እጅግ የኢትዮጲያን ህዝብን መናቅ ነው። ምን ዋጋ አለው የታልቁን

*መሪ ራዓይ ብቻ እንደሚተገብሩ እንጅ ምንም ለውጥ እና ማስተካከያ እንደማይኖር በዲፍረት በኢትይኦጲያ መግናኛ ኣግልግሎት ተገልጽዋል።*

*ግን፡- እንዳላሉን ሁሉ ነኝ ተጋዳላይ፡*
*ለዴሞክራሲ እና ለነጻነት ጉዳይ፡*
*የህዝብ ብሶትን እንባን እጠርግ ባይ፤*
*ኣድርጎ እራሱንም የህዝብ ተወካይ፤*
*መገናኛን ሊያደርግ የህዝብም አገልጋይ፤*
*ቃሉን በላው እንጂ ያውም ባደባባይ፤*
*በፊትም አሁንም ዓለምን አታላይ፡*
*ማበል ኣያዋጣም ያስጠይቅሃል ቆይ፤*
*መዘዙ ያውልህ ያውም ማሰቢያህ ላይ፡*
*ዋ! እሆነለሁ ብትል የዋሾ ተከታይ፤*
*እውነት ጦርም ሁኖ ይወጋሃል አባይ።*



አልፎ ተርፎም ደግሞ ለሆዳቸው ባደሩ ጋዜጠኞች እና ደህንነቶች የፖለቲካ ተቃዋሚ ኃይል ተወዳድሪውችንም ሆነ ነጻ ጋዜጠኞች "**አኬል ዳማ**" እና ድምጻችን ይሰማ ያሉ የሃይማኖት ተከታዮች የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎችን "**የጀሃድ ሃረካት**" በሚል ህግን በመጣስ ድራማ እያቀናባበሩ በኢቲቪ (ETV) ለህዝብ ተላለፉዋል። አቶ በረከት ስሞኦን የሚያዙት የኢትዮጲያ ቴሌቪዥዎን እና ሬድዮ ገና በተጠርጣሪ ጥፋተኛ ታሳሪዎች ላይ የሃሰት ታርጋ በመለጠፍ ሕዝብን ለማጋጨት መርዙን ለህዝብ መርጨቱን ተያይዞታል። የኸውእና እኛ ኢትዮጲያኖች በወያኔ-ኢሕአዴግ የሰላም ተስፋችን ተሞጦ የመንግስት ሃላፊነትን በትክክል የሚውጣ መሪ እና ነጻ የመገንኛ ቡዙሃንም እንደናፈቅን 22ኛው ዓመት እንበለው ወይስ የስራዓቱ መገባደጃ 11ኛው ሠዓት ላይ እንገኛለን። የኢትዮጲያ ህዝብማ ምን ኣልባት የህዝብ መግናኛ አግልግሎትን እንኳን ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጠርን ብለው ከተናገሩ ኣይቀር ቃላቸውን ከጠበቁ እንዲሁም የትግሉ ጥያቄ በህገ መንግስቱ መሰረት ስለሆነ በሰላም ሊከበር ይችል ይሆናል ተብሎ እንጅ ሃገሩን እየሸንሸነ ከሽጠ እና ህዝቡን በዘር ከፋፍሎ የውሸት ኣውራ ፓርቲነት ነኝ እያለ ከሚገዛ መንግስት ነኝ ባይ ወንበዴ ምን ጥሩ ምላሽ የጠበቃል።

ለምሳሌ ቢጠቅስ ኣናንተ የኢትዮጲያ ህዝብ ሆይ የ1997ቱ በሰላማዊ መንገድ የኢትዮጲያ ፓርላማ ተወካዮቻችሁን ለመመረጥ ያደረጋችሁት የፖለቲካ ህብረት፡ የነቃ የፐሊቲካ ተሳትፎ እና የዲሞክራሲ ለውጥ ፍላጎት ርብርብ እንዲሁም በዘርም ሆነ ባኣካባቢ ሳትከፋፈሉ "በድምጻችን ይሰማ" ለሃይማኖታችሁ መከበር በያደባባዩ ለርዥም ጊዜ ያሳያችሁት የሰላምዊ ሰልፍ ትግል እንዲሁም ትክክለኛ እና ህጋዊ የፓትርያርክ ምርጫ ለማድረግ በተደጋጋሚ የተደረገው በክርስቲያን አባቶች የተመራ የእርቅ እና የሰላም ጉባአኤ እጅግ ኣለምን ኣስደማሚ እና ሰላማዊነትን የተጎናፀፈ ነበር ማለት የሚያስደፍር ነው።

***ሁኖም ግን ለሃገሩ እና ለህዝቡ የቆመ ኣልፎ ተርፎ እራሱ ያፀደቀውን ህግ-መንግስት የሚያከብር ገዥ ባለመኖሩ ያለ ተጨባጭ መፍትሄ በመንግስት ነኝ ባዩ ወያኔ/ኢሕኣዴግ ሕዝባዊ ትግላችሁ በግትረኝነት መክሸፉ መዘዙ የከፋ እንዳይሆን ያስፈራል።*** *ኣልፎ ተርፎም የሰው ልጅ ህይወት መስእወትነት*

ኣስከፍሎዋል። ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ ብሎ መልሶ ያበሰብስል እንደተባለው ሁሉ ሃገር ሊያፈርስ እና ህዝብን ሊያራርቅ የተቀመጠ መንግስት ነኝ ባይ ጆሮ ዳባ ብሎ የሰላም ትግልህን ኣምክኑዋል። ለዴሞክራሲ እና ለሰላም ብትጮህም ሆነ ብትደክም ሰሚ የሃገር መሪ ስለሌልህ እጅግ ጉዳት ደርሶብሃል። ሃገር እና ሰላም ወዳጁ የኤትዮጺያ ክርስትያን እና ሙስሊም ማህበረሰብ ሆይ ስንት የሚያንገበግቡ እና በኣቢዮታዊ ዲሞክራስያዊ መርህ ስም የታፈኑ የሃገር ጉዳዮች እያሉ የወያኔን መንግስት የጠይቀችሁት እራሱ ፅፎ እራሱ ባጸደቀው ህገ-መንግስት መሰረት በመረጥኩት የፖልቲካ ድርጅት ወይም በተቀበልኩት የፖለቲካ ርዓዮተ ዓለም ልመራ እና በምነቴ መንግስት ጣልቃ ኣይግባብኝ የሚል ግልጽ እና ህጋዊ መብትን ነበር። ነገር ግን ከቀናቶች ሳምንቶች ብሎም ወሮች ከዚያም ኣመታቶች ቢቆጠሩም ከወያኔ ቡድን ምንም የሰላምዊ መፍትሄ እስካሁን ኣልተገኘም ይገኛል የሚል ፍንጭም የለም።

በተጨማሪም ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወድያ እንደተባለው ሁሉ የወያኔ ባለስልጣን ተገቢ ሕጋዊ ምላሽ መስጠት ሲገባው በኣደባብይ በፀረ ሰላምነ ወንጅሎ ኣሸብሮችሁውል። ኣልፎ ተርፎም በታጣቂ ያለርህራሄ ወዳጆቻችንን ገሎብናል፤ ተወካዮቻችሁን እስር ቤት ኣጉሮ ኣንገላቶባችሁዋል። ያለስርዓት በሚፈነጭበት [የህዝብ ሚድያ ተጠርጣሪን በካቲና ኣስሮ እና ሰባዊነትን ገፎ በማስፈራራት መርማሪዎች እየተሳለቁ ለድራማ] ሲያዘግጁላችሁ በኢትዮጺያ ቴለቪዥን ኣገለግሎት (ETV) ተላልፉዋል፡፡ በተሰለፉችሁበት የሰላም ሜዳ ሚዛናዊ ያልሆነ መረጃ እየተዘገበ እና በብቸኝነት በሚቆጣጠረው ሚድያ ለህዝብ እያቀረበ ኣድናግሩዋችሁዋል።




የሰው ልጅ ከኛ ጋር እያለ በነፍሱ፤
ኣያሳዝንም ወይ በሙት መደረሱ፤
ዛሬንም መዋሸት ነገንም እንደዛው፤
ያውም ባደባባይ በኢትቪ ተብየው፤
የኸው ስም ተሰጠህ ተባልክ ጥሩንባው፤
ባደራም ተከለልክ ማንም እንድይነካው፤
ሙያ ክብር ነበር ቃል የገባኽለት፤
ሚዛናዊ ዜና ልትዘግብበት ፤
ይቅርልህ ጥሩንባው! ተባል ጋዜጠኛው!
ኢትዮጺያን ኣገልግል ቃል እንደገባኸው፤

ሰው በሃገሩ ላይ እንዳልባሌ እስከ ጋዜጠኛው ጭምር የህሌና ኣሰቃቂ ግፍ ተሰርቶበታል። እንደ ጭድ እና ጭቃ ተዋህዶ የኖረውን ኢትዮጺያዊያን በዘር ለመከፋፈል፤ ክርስቲያን እና ሙስሊሙን ህብረተሰብ ለማጋጨት ተንኮል ተሸረቡዋል፡፡ በኣንጻሩ ግን እጅግ በሚገርም ሁኔታ በማንም ላይ እስካሁን ጣታችሁን ሳትቀስሩ በሰላም ትግስታችሁን ኣሳይታችሁዋል፡፡ በዘር እና በኣሉብልታ ሳትከፋፈሉ በመቻቻል ለዘመናት ኑራችሁን ባንድ ጋ ገፍታችሁዋል። በሃገርህ ላይ ኣሻፈርኝ (ሆድ ባሰኝ) ብላችሁ ጫካ ስትገቡ ኣሁንም ትክክለኛ የሕዝብ ምርጫ ይደረግ እንዲሁም ህገ-መንግስታዊ የመብት ድምጻችን ይሰማ ትላላችሁ። በውነት ሰላም ወዳጁ የኢትዮጺያ ህዝብ ያኮራል፡- ስሜታዊ እና የጥላቻ ሃሴት ተጠናውቶ በዓለም እንዳየነው በወገንህ ላይ ቦንብ መጣል እና በሃገርህ ላይ ደግሞ የምሽግ ቁፋሮ ኣለመጀመሩ ያስደንቃል። ይህ ነው እንግዲህ እልህ ኣስጨራሽ የሰላማዊ ትግል እና በታጋሽነት የተሞላ

ኢትዮጲያዊ ጨዋ ህበረተሰብ ማለት። መንግስት ተብየ እንዳለው የኢትዮጲያ ህዝብ አክራሪ ሳይሆን ኢትዮጲያዊ ጨዋነቱን እና ሃገር ወዳድነቱን ለዓለም ሕዝቦች በሰላማዊ የተግል ሜዳ በተደጋጋሚ በግልጽ አሳይተዋል ማለት ይቻላል።

ያለ መታደል ሆኖ መንግስታዊ መዋቅሩን በዘር ሃረግ መስርቶ እና ኢትዮጲያን ተቆጥጣጥሮ ያለው ወያኔ ከአፈጣጠሩ እስካሁን በሄደበት መንገድ ሲመዘን በውስጡ ቅንጣት ያህል የዴሞክራሲያዊ ባህል የለውም። ምክንያቱም ዴሞክራሲያዊ ባህል የዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዐትን መዳበር ወይም አለመዳበር ከአንድ መንግስታዊ ይዞታ አንጻር የሚመረመር ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነው። ዴሞክራሲ ሕዝብን ተቆጣጣሪና ኃያል የሚያደርግ በተቃራኒው ደግሞ አምባገነናዊነትን ጥቂት ገዥዎችን አገልጋይና ታዛዥ የሚያደርግ እሳቤ ነው። ሂደቱ መሠረታዊ እምነትን የአመለካከትንና ይዞታዊ ሕልውናን የሚያመለክት ነው። ከዚህ አንጻር የወያኔ ሥርዐት ዴሞክራሲያዊ ባህሉ የለውም የምንለውም የመንግስታዊ መዋቅሩ ሕዝብን ሊገዛ እንጂ ሊታዘዝ፤ ሊረግጥ እንጂ ሊያገለግል የሚችል መዋቅራዊም ሆነ የዕምነት ብቃት የለውም። የመንግስት መዋቅሩ ለሕዝብ ግልጽና ተጠያቂ አይደለም ምክንያቱም ሕዝባዊ መሠረት የለውምና። ሰለዚህ ለሰላማዊ ጥሪ ሁል ጊዜ መልሶ የተዛባ ሆኖ ታይትዋል።

ሰላም ወድዱ የኢትይኦጲያ ህዝብ ሆይ "ያገኘውን በልቶ ወሃንም ጠጥቶ የትኛውን በሬ ፡
ተንኩሰው ቀስቅሰው አደርጉት አውሬ" እንደተባለው ሁሉ
ከንግዲህ የሰላማዊ ትግል ውጤቱን እና የወያኔን የጥላቻ መልስ ምት በተገቢው ሰላያችሁት በምላሹ እናንተም እንቢ ልትሉ ይገባል። ለህጋዊ እና ቀላል የመብት ጥያቄ እንኳን መልስ ለመስጠት ወያኔ አልፈለገም። ይባስ ብሎም ቤትህ ድረስ በመምጣት ፍተሻ እያከሄደ እና እየዘረፍህ ተተንኩሱሃል። ነጻ ጋዜጠኞችንም ጭምር የፖሊስ አዣዥ ተብየው ዋሽንግተን አይደለም መንግስተ ሰማያት መጠቻ እወስዳለሁ አሁኑን በማለት ሲያስፈራሩ [በአሜሪካ ዲምፅ ሬድዮ (VOA)] ተሰምቱዋል። አሳሳቢው እና አሳዛኙ ጉዳይ ሃሳብ በነጻ ከሚንሸራሸርበት አሜሪካ ድረስ በመምጣት ጋዜጠኛውን እቀጣሃለሁ በማለት የዛተ ፖሊስ አጠገቡ ያለውን የኢትይኦጲያ የታፈነ እና ጭቁን ህዝብ የቱን ያክል ሊያንገላታ እንደሚችል ሲገመት ነው። በመሆኑም በጨለማ ላይ ቢፈጠር ምንም የሚታይ እንደሌለ ሁሉ በህዝብ ላይ የጥላቻ ፖሊቲካ ከሚያራምድ ወያኔ በጎ እና ህገመንግስታዊ ምላሽ ከመጠበቅ ይልቅ አምርረህ ልታምፅ እና ልትታገለው ይጋባል።

ከንግዲህ ወድያ "ትመር እንደሆነ ምረር እንደ ቅል፡
አልመር ብሎ ነው ዱባ እሚቀቀል" እንደተባለው ሁላችንም የዱባው እጣ እንዳይደርሰን በመጠንቀቅ እንታገል። እስካሁን ያካሄድከው **የሰላምዊ ትግል እጅግ አስደማሚ ቢሆንም** ለወያኔ የገባው ስለማይመስል ቻይነትህን ካሳየኸው የአስተዳደር እጦት እና ግፍ አንግፍግፎት በዓለም እንደ ጎመን ዘር ከተበተነው የዳስፖራው ወገንህ ጋር በመተባበር የትግል አቅጣጫህን ልትቀይር እና ወያኔን በመፋለም ልታስወግደው ግድ ይላል።

ስለሆነም የክርስቲያን በዓል ገናን አብረህ ተቆራቁሰህ እና ተጫውተህ እንዲሁም የሙስሊሙን ዓረፋ እና ፍች ቡና በመጠጣት በመከባበር ተመራርቀህ እና ተቻችለህ የኖርክ ወገኔ ሆይ የሃገርህን ሉዓላዊነት እየሸጠ እና ሰብዓዊነትህን እየረገጠ ባለው የወያንኔ ቡድን ላይ ባንዲነት በማመፅ ክብርህን ለማስመለስ

ሳይመሽ ቆርጠህ ልትነሳ ይገባል። የወያኔ-የኢሕኣዲግ ሻዥ ከንግዲህ ህዝብን እያደኸየ ነገር ግን እራሱን እያገዘፈ እንዲሄድ የሚጠቀምበትን የኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተ ዓለም  ፖለቲካ እና ፕሮፖጋንዳ በመገናኛ ብዙሃን እየረጨ ሊቀጥል ኣይገባም። ብሶተኛው የወያኔ/ኢሕኣዲግ መዥገር የሰፊውን ህዝብ ደም እየመጠጠ ሁሉን ሆድ ስላስባሰው ባንድ ጋ እንደተለመደው ሰፊው የኢትዮጲያ ህዝብ ከንግዲህ በቃ ብሎ በመተባበር ነቅሎ ለመጣል የኣመጽ ትግል ወሳኝ ነው።




የሰው ልጅ ሁሉ በደል ሲበዛበት ብሶት እንደሚሰማው ሁሉ በመደራጀት የሰፊው ህዝብ ትግል ከዳር እስከደር ባንድነት ተቀጣጥሎ ዘርኝው እና ከፋፋዩ መንግስት ነኝ ባዩ ተወግዶ ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም ሁልችንም የበኩላችንን ትግል ለማድረግ ቆርጠን እንነሳ። ያለ ድርጅት ትግል ያለትግል ድል ከቶም አይታስብምና እንዲሁ ሁኔታዎች በተፈጠሩ ውቅት ብቻ እየተነሱ ደወል ከሚያቃጭሉ አስመሳይና ወላወይ ከወያኔ ጋር በተለያየ መልኩ  ያላቸውን ቁርኝት ያልበጠሱ ፣ ከምዕራቡ ዓለም ቡራኬና መመሪያ ከሚቀበሉ ፣ ከዚህ በፊት ከወያኔ ጋር ሆነዉ ሕዝብንና ሀገርን ሲጎዱ ከነበሩ፣ የሕዝብንና የአገር ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የጣሉ ወይንም በኢትዮጵያችን ህለውና ላይ ብዥታ ያለባቸውን እየለየን፣ ሰልፋችንን ከሕብረ ቤሄራዊ፣ ብሎም የጎድፈ ታሪክ ከሌላቸው ፣ በጽናትና በቆራጥነት ለዘመናት በመታገል  ሕዝባችን የሥልጣን ባለቤት ላማረግ በትግል ላይ ያሉትን፣ወያኔን የአገርና የሕዝብ ጠላት ነው ብለው ከቆረጡ፣ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ከሚያምኑ ጎን በመሰልፍ ትግሉን ብናፋጥነው እና ብናቀጣጥለው ለድል እንደምንበቃ አንጠራጥርም።

ከንግዲህ ምከረኽው ዘክረኸው ወያኔን ስላልገባው ወሳኝ እና መራራ ምእራፍ ላይ በመድረስህ መከራው እንዲመክረው ለማድረግ ንቃ፡ ተደርጅ፡ ታጠቅ፡ ከዚያም በሃገርህ ጥላት ላይ ነጥለህ በመዝመት የሰላም መንገድ ፀረኛው ውያኔ መዘዙን ሊደርሰው ይገባል። የነቃ የተደርጀ እና የታጠቀ ሕዝባዊ ኣብዮታዊ የኣመጽ ትግል ምንጊዜም አሸእናፊነቱ ጥርጥር የለውም።  የተገዳልዩን የመጀመሪያውን የሬድዮ ቃል ኪዳን የመገናኛ ብዙሃንን ለሰፊው ህዝብ ጥቅም በትክክለኛነት በተግባር ለማዋል እና ነጻ ኣስተሳሰብን ለማስፈን የዋሾውን ወያኔ-ኢህኣዲግ መጨርሻ እናፋጥነው። ለድሞክራሲ፡ ለሰላም፡ ለፍትህ፤ እንዲሁም ሃቀኛ የመገናኛ ብዙሃኖችን ለሰፊው የኢትዮጲያ ህዝብ ጥቅም እንዲውሉ ጭምር ሌላ **ኣስደማሚ እና ውጤታማ ህዝባዊ አብዮታዊ የትግል ስልት**  በሰፊው ህዝብ ውስጥ ሊሰርፅ እና ሊያብብ ወቅቱ ግድ ይላል ። ስለዚህ ሁላችንም በአንዲነት ለድሞክራሲያዊ ትግል እንደምንነሳ አንጠራጠርም። የሰው ልጅ የስባኣዊ መብት የትም ይከበር! ኢትዮጲያ በሀቀኛ ልጆችዋ ጥረት በአንድነት ጸንታ ትኖራለች!!

ድል ለኢትዮጲያ ሰፊ ህዝብ! ይሁን – አሚን!!!

ኢትዮጲያ ለዘላለም ከነክብሩዋ ትኑር!

በያቆብ ተክሌ ኣርጋው - ከኖርዌ